# *የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ-ማህበራት ጉባኤ (ኢሕማጉ)*

# *Congress of Ethiopian Civic Associations (CECA)*

## ለአማራ የህልውና ትግል የተሰጠ የድጋፍ መግለጫ

በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ የሰው ልጆች ክብራቸውንና ነፃነታቸውን ሙሉ በሙሉ ተገፈው ለከባድ ሥራ፤ እንግልት፤ ግርፋት እሥራትና ስደት ከተፈራረቀበት የባሪይ አገዛዝ ተብሎ ከሚጠራው ሥር ዓት የከፋ ያለ አይመስልም።

ዛሬ በአገራችን በአማራው ህብረተስብ ላይ ግፈኛው የአቢይ/ብልጽግና አገዛዝ በማድረስ ላይ ያለው አንድን ዘር ነጥሎ የማጥፋት እርምጃ በትውልዳችን ከተከሰቱት ኢሰባዊ ድርጊቶች የሚተናነስ ሳይሆን የከፋ ነው።

ለአማራው ማንነት፤ ህልውና፤ መብትና ፍትህ መከበር ብለው ከአማራው አብራክ የወጡ ልጆቹ (ፋኖ፤ የክልሉ ታጣቂ ሀይል) የሚያድርጓቸው ትግል፤ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አመጽን ከወለደ ውሎ አድሯል።

በመሆኑም የአማራው ህብረተሰብ ከስላማዊው ሕዝባዊ ንቅናቄ ጀምሮ ተገዶ እስከገባበት የትጥቅ ትግል ህልውናውን ለማስከበር የሚደረግ ህጋዊ ትግል በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ባርነትንና የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋውን የሚቃወሙ የዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ሙሉ ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል ብለን እናምናለን።

የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ-ማህበራት ጉባኤ (ኢሕማጉ) የተቋቋመው በኢትዮጵያዊያን ማዕቀፍ የተደራጁ የዲያስፖራ ሕዝባዊ ድርጅቶች በመተባበር ሀገራችን ከዘረኛና ፋሽሽታዊ አገዛዝ ተላቃ ፍትህ፤ እኩልነትና ብልጽግና የሰፈነባት ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚድረግ ሀገር በቀል ርብርብ አጋር ለመሆን ነው። በዚህ መሠረት በተለየ ታላቁና ትልቁ የአማራ ሕዝብ በወያኔና በኦነጋውያን የታወጀበትን ዘር ማጥፋት ዘመቻ ለመቋቋም ከእልክ አስጨራሽ ትዕግስት በኋላ እያደረገ ያለውን አትንኩኝነትና እራስን የመከላከል ጥረት እንደምንደግፈው እንገልጻለን።

1ኛ) ብሶት የወለደውን የአማራ የህልውና ንቅናቄ በሙሉ ልብ እንደግፋለን፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ የተጠነሰሰለትን ተመሳሳይ ጥቃት በተረኝነትና በግብዝነት መጠበቅን አቁሞ ከአማራው ጋር እንዲሰለፍ አስቸኳይ ጥሪ እናቀርባለን።

2ኛ) በቅርቡ የዐማራ ሕዝባዊ ግንባር (Amhara Popular Front) መመሥረቱን እንደ የምሥራች እናየዋለን፤ ተጠያቂነትና ጥራት ያለው  ድርጅት እንዲገነባ ትልቅ ጉጉታችንና ምኞታችን ነው።

3ኛ) በሕዝብ እምቢተኝነትም ሆነ በትጥቅ ትግል ስልት የሚመሩ ሌሎች የዐማራ ስብስቦች እንዳሉም እንገነዘባለን። ስለዚህ ባደባባይ የወጡትና በህቡዕ የሚሰሩት የዐማራ ድርጅቶች ቢያንስ እየተከባበሩና እየተናበቡ ቢቻል ደግሞ በአንድነት እንዲሰለፉ እንማፀናቸዋለን። ፍኖተ ካርታ ነድፈው ዐማራነትንና ኢትዮጵያዊነትን አዋህደው እንዲንቀሳቀሱ ከመምከር አልፈን የተቻለንን የሀሳብና የቁሳቁስ ድጋፍ እንደምናበረክት ልንገልጽላችሁ እንወዳለን።

‘መነሻችን አማራ መዳረሻችን ኢትዮጵያ’ በሚል መርህ ሥር የተደራጁ  የአመራሩ የቁርጥ ቀን ልጆች ትግል በድል እንዲጠናቀቅ የድርጅታችን ልዩ ትኩረት እንደማይለየው እናሳውቃለን።

**የዐማራ ሕዝብ ፍትህን በቅርቡ ይጎናፀፋል፤ ኢትዮጵያንም ይታደጋል።**

<u>የኢትዮጵያን ሕዝባዊ ድርጅቶች ጉባኤ አባላት፤</u>

1. እምቢልታ/አገር አድን ኅብረት (Embilta)
2. ግሎባል አሊያንስ(GLOBAL ALLIANC FOR THE RIGHTS OF ETHIOPIANs
3. የኢትዮጵያ የውይይት እና የመፍትሄ መድረክ(EDF)
4. ቪዥን ኢትዮጵያ (VISION ETHIOPIA)
5. የዲሲ ግብረ ሃይል (DC Task Force)
6. የኢትዮጵያ ሴቶች መብት ማእከል(CREW)
7. አለምአቀፍ የኢትዮጵያዉያን የሲቪክ ድርጅቶች ኔትዉርክ (WE CAN)
8. ኢትዮጵያዊነት የዜጎች መብት ማስከበሪያ ድርጅት
9. ልዩ ልዩ የኢትዮጵያዋን ተቆርቋሪ ስብስቦች (concerned Ethiopians)
10. ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያን ሴቶች ማህበር (Intl Ethiopian Women’s Assn.)